# ምዕራፍ ሁለት፡- ተከታዩ ተግባር

## ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
### የተሰጠ መግለጫ

ሰኔ 20 ቀን 2000 ዓ. ም. (June 27, 2008)

ይህ ኮሚቴ ባለፉት ብዙ ወራት የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ርዝመቱ 1600 ኪሎ ሜትር ጥልቀቱ ደግሞ ከ30 እስከ 60 ኪሎ ሜትር የሚደርስ ውሃ ገብ ለምና የማዕድን ክምችት መሬት ለሱዳን ሲያስረክብ እጅ ከፍንጅ እንዲያዝና ሴራውም ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲጋለጥ አድርጓል። ከማጋለጥ ማዶ የሚከተሉት አጀንዳዎች ለምናደርጋቸው የድንበር ጉዳይ እንቅስቃሴዎች ዋና ንድፎች ይሆናሉ።

1. የተጀመረው የማጋለጥ ዘመቻ በደመቀ መልኩ መቀጠልና የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔ/ኢ.ሕአዴግ የሚፈጽመውን ሥውር የመሬት ማስረከብ ሴራ አበክሮ እንዲገነዘበው ማድረግ፤

2. ስለድንበሩ ጉዳይ የሕግና የታሪክ ባለሙያዎች የተሳተፉበት ቡድን ጉዳዩን አቀነባብሮ ለዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ተቅዋማት ማድረስና በሕግ በኩል ዘለቄታ ያለው የዳር ድንበር ማስከበር ሥራን ማከናወን፤

3. ወያኔ/ኢ.ሕአዴግ በድንበሩ አካባቢ እየፈጸመ የሚገኘውን የሕዝብ ማንገላታት፣ የማሠርና የመግደል ዘመቻ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም ኅብረተሰብ ማጋለጥ፤

4. በሱዳን ወረራ ምክንያት ከእርሻቸውና ከመንደራቸው የተፈናቀሉ በጋምቤላ፣ በወለጋ፣ በጎጃምና በጎንደር ክፍለ ሀገራት የሚገኙ ወገኖቻችንን እርዳታ እንዲያገኙ ማድረግ፤

5. በሱዳን ወታደር ታሥረው ሔደው መዳረሻቸው የጠፉ ስድስት(6) ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችንን ጉዳይ ማወቅና እርዳታ ማቅረብ፤

እነዚህ ዐበይት የተግባር ዕቅዶች ዘለቄታ ያለው ውጤት ሊያገኙ የሚችሉት ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሀገራችንን ሉዓላዊነት እንደተቀዳሚና መሠረታዊ ጉዳይ አድርጎ ሲይዘው፤ እንዲሁም በቆራጥነትና ባለመሰልቸት ከሀዲዎችንና ኀሊና-ቢስ ሆዳሞችን እያሳፈረ ወደፊት ሲገፋ ነው። ስለዚህም ከላይ የተጠቀሱትን ዕቅዶች በአመርቂ መልኩ ከተፈለገው ቦታ ለማድረስ የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ትብብር እንጠይቃለን።

የተግባራችን ሂደት ከግል ቆራጥነት አልፎ አንድነትና እጅ ለእጅ መያያዝን ስለሚጠይቅም በየትም ከተማና አገር የምትኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ በያላችሁበት ኮሚቴ በማቋቋም በተወካዮች አማካይነት እየተገናኘን በአንድነት እንድሠራና የያዝነውን ተግባር ዳር እንድናደርስ አደራ እንላለን።

- ምክር፣ አስተያየት ወይም ሙያ-ነክ እርዳታ ለማበርከት የምትሹ በሚቀጥሉት አድራሻዎች ልታገኙን ትችላላችሁ።

  e-mail: ethiosudanborder@yahoo.com
  Ethiopia-Sudan Border Affairs Commitee
  P. O. Box 656
  Tucker, GA 30085 USA

- ለተፈናቀሉ ወገኖቻችን እርዳታ ለማበርከት፤ ድንበሩን በተመለከተ ለሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉ የገንዘብ አስተዋጽኦ ለማድረግ የምትፈልጉ በሚቀጥለው አድራሻ ልትልኩልን ትችላላችሁ።

  Wachovia Bank
  Routing number: 061000227
  Account number: 2000040737593
  OR
  Send Check or Money Order payable to:
  Ethiopia-Sudan Border Affairs Commitee
  P. O. Box 656
  Tucker, GA 30085 USA

ወገኖቻችንን ለመርዳት በአንድነት እንነሣ!
ኢትዮጵያ በክብሯ ለዘለዓለም ትኑር!

የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ